በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

በጣና ሃይቅ ደሴቶች ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ገዳማት

በኢትዮጵያ ትልቁ በሆነው ሃይቅ ዙሪያ በታሪክ ሃብታም የሆኑ በርካታ ገዳማት ይገኛሉ። ከእነዚህ ገዳማት አንዳንዶቹ ከ 700 አመት ዕድሜ በላይ ያላቸው ሲሆኑ በውስጣቸው ከተለያየ የሃገሪቱ ክፍሎች የተሰባሰቡ ውድ የታሪክ ቅርሶችና የመካከለኛው ዘመን የሃገሪቱ ነገስታትን አጽም የያዙ ናቸው።

በመሆኑም ገዳማቱ በተለያዩ ጎብኝዎችም ሲጎበኙ ይስተዋላሉ።

ደቅ ደሴት **(Dek Island)**

ይህ ደሴት ጣና ሃይቅ ካሉት ደሴቶች ሁሉ ትልቁ ደሴት ሲሆን ከባህር ዳር ከተማ 37 ኪሜ ርቀት ላይ ይገኛል። በዚህ ደሴት ውስጥ 7 (ሰባት) አድባራትን የያዘ እና "የሰባት ደብር አገር" በመባል ይታወቃል። እነዚህም ደብሮች በስም ዳጋ እስጢፋኖስ፣ ናርፋ ስላሴ፣ ቅድስት አርሴማ፣ ኮታ ማርያም፣ ዝባድ ኢየሱስ፣ ጀጋ ዮሃንስ እና ጋደና ጊዮርጊስ በመባል ይታወቃሉ።



ደቅ ደሴት



ናርጋ ስላሴ

ደቅ ስላሴ መጀመሪያ ለመነኮሳት ብቻ እንጂ ለአላማውያን የተከለከለ ደሴት ነበር። እየቆየ ግን ቀስ በቀስ ሰዎች ወደ ደሴቱ በመምጣት፣ በመስፈር እና በመዋለድ የኗሪው ቁጥር ከፍ ሊል ችሏል ። በአሁኑ ጊዜ የደሴቱ ነዋሪዎች የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ናቸው። ወደ ደሴቱ የአለማውያን መግቢያ ዘመን በአራት ተከፋፍለው ይነገራሉ

፯- የግራኝ አህመድ ጦርነት ጊዜ

፰- እቴጌ ምንትዋብ የናርጋ ስላሴ ቤተክርስቲያንን በሚያሰሩበት ጊዜ

፱- በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት

፲- በአፄ ዮሃንስ 4ኛ ዘመነ መንግስት በነበረው የደርቡሾች ወረራ ወቅት

ክብራን ገብርኤል እና እንጦሥ **(Kibran Gebriel and Entoss)**

እነኝህ መንትያ ደሴቶች ከባህር ዳር ከተማ በስተ ሰሜን ማዕራብ በጀልባ የ 45 ደቂቃ ርቀት ላይ የሚገኙ ሲሆን የደሴቶቹ መልከዐምድራዊ አቀማመጥ እና የተሸፈኑበት አረንጓዴ ደን እጅግ ውብ አድርቸዋል።

ክብራን ገብርኤል ገዳም የወንድ ብቻ ገዳም ሲሆን እንጦስ ገዳም ደግሞ የሴቶች ብቻ እንደነበር ይነገራል። ይሁንና በእንጦስ ገዳም ያሉ ሴቶች በተለያዩ ምክንያት በመሰደዳቸው በገዳሟ ላይ የኢየሱስ ገዳም ገብቶ የወንዶች ብቻ ሆኗል።



ክብራን ገብርኤል


የክብራን ገብርኤል ደሴት መጀመሪያ የተሰራው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት ሲሆን በዳግማዊ ዳዊትና ከዚያም በአዲያም ሰገድ እያሱ እንደተሰራ ይነገራል። ቤተክርስቲያኑ በልክ በተጠረቡ ቀያይ ድንጋዮች የተሰራ ሲሆን በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ከድንጋይ የተጠረቡ 12 አምዶች ይገኛሉ። በገዳሙ ውስጥ እና በአፄ ፋሲል እንደተሰራ በሚነገርለት እቃ ቤት ከሚገኙት ዋና ዋና ታሪካዊ ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

- ✓ ከቤተክርስቲያኑ መቅደስ ግድግዳ ጋር ተያይዞ በተሰራ ክፍል ውስጥ የገዳሙ መስራች የአቡነ ዘዮሃንስ መቃብር
- ✓ በሃዋርያው ሉቃስ እንደተሳለች የሚነገርላት ስዕለ ማርያም
- ✓ ከብረት የተሰራው የአቡነ ተክለሃይማኖት ተደራራቢ አልጋ
- ✓ ከእንጨት የተሰሩ መቅረዝ እና አገልግል
- ✓ መስቀሎች
- ✓ የገበታ ላይ ስዕሎች

- ✓ የብራን መፅሃፍት

ዘጌ ባህር ገብ **(Zeghe Peninsula)**

የጣና ሃይቅ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ በመግፋት ተንሰራፍቶ የሚታየው ባህረገብ መሬት ዘጌ በመባል ይጠራል። ዘጌ ከባህር ዳር ከተማ 15 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ነው። በዚሁ ባህረ ገብ ላይም 7 የሚሆኑ አብያተ-ክርስቲያናት ይገኛሉ። በስምምነ- መሃል ዘጌ ጊዮርጊስ፣ አቡነ በትረማርያም፣ አዝዋ ማርያም፣ ውራ ኪዳነምህረት፣ ደብረስላሴ፣ ይጋንዳ አቡነ ተክለሃይማኖት እና ፋሪ ማርያም በመባል ይታወቃሉ።



ዘጌ ባህር ገብ በፀሃይ ጥልቀት

ደብረ ማርያም **(Debre Mariam)**

ከባህር ዳር ከተማ በሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በጀልባ የ 20 ደቂቃ ወይም በእግር የአንድ ሰዐት ተኩል እርቀት ላይ የምትገኘው ደሴት ላይ የምትገኝ ገዳም ስትሆን ይቺ ገዳም በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት (1307-1337 ዓ.ም) እንደተመሰረተች ይነገራል። ገዳሟ ያለችበት አካባቢም በሁለት ተጨማሪ "ጉማሬ ባህር (በአካባቢው ብዙ ጉማሬዎች ስለሚገኙ) እና አባይ ራስ (የአባይ ወንዝ የጣና ሃይቅን ውሃ ሰንጥቆ የሚወጣበት ቦታ በመሆኑ) በሚሉ ስሞች ይታወቃል።

ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ፣ ጥንታውያን ገዳማት

እና አድባራት ታሪክ በኢትዮጵያ